በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

**ታህሳስ 27 ቀን 2011**
**አዲስ አበባ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመምህራን ጋር ተወያዩ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ 3,696 መምህራን ጋር ዛሬ ታህሳስ 27 ቀን 2011 በጽህፈት ቤታቸው ተገናኝተው ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢን በመፍጠር ዙሪያ ከመምህራኑ ለተነሱላቸው በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ከመምህራን ጋር የተደረገ ውይይት ትውልድን ኮትኩቶ የማሳደግ የመምህራንን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት የተካሄደ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለፁት አገር ወዳድ ዜጋ ማፍራት መምህራን ለአገር ግንባታ የሚጥሉት መሰረት ውጤት ነው።

ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎችና ችግሮች ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል፦

**የትምህርት ጥራት ማሻሻያ:** መንግስት የአገሪቱን የትምህርት ስርዓትን ለማሻሻል የሚደረጉ ጥረቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠሉ ማሳያም የትምህርት ሚኒስትርን ለሁለት በመክፈልና እንደገና በማዋቀር ብሎም በሁሉም ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች በትምህርት ዙሪያ ውይይቶች መካሄዳቸው ይጠቀሳል።

**የመምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም:** የመምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ማሻሻያ በትምህርት ሚኒስቴር እየተከለሰና እርማት እየተደረገበት ሲሆን ይህም በታላቅ የእዳ ጫናና አመታዊ የበጀት መጠኑን ከፍ ለማድረግ እየተሞከረ የሚገኘውን የአገሪቱን የማክሮ ኢኮኖሚ እውነታ ማገናዘብን ይጠይቃል።

**የመምህራን ሰላምን የማስፈንና የማስጠበቅ ሚና:** መምህራን የሚመጣላቸውን መረጃ አጣርተውና መርምረው ከግልፍተኝነት ይልቅ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ላይ የሚደርሱ ዜጎችን የማፍራት ኃላፊነት አለባቸው። የውይይትና የክርክር ባህልን በማዳበር: የግጭት አፈታት ዘዴዎችንና የፆታ: የብሄር: የሃይማኖት እኩልነትና ልዩነትን የመገንዘብ የትምህርት ሂደት አስፈላጊነት ተነስቷል። ይህንን በማድረጋቸው መምህራን 4ቱን የሰላም ግንባታ መርሆዎች ይተገብራሉ። እነሱም መልሶ ማከፋፈል፣ ማስታረቅ፣ እውቅና መስጠትና ውክልና ናቸው።

**ፀጥታ:** በአሁኑ ወቅት መንግስት የለውጥ ማሻሻያዎችን በመተግበር ኢትዮጵያ ቀድሞ ትታወቅበት ከነበረው የኃይልና የጭቆና አገዛዝ ለመለወጥ እየጣረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይህ ዲሞክራሲያዊ ቻይነት መንግስት ደካማ ነው በሚል መወሰድ የለበትም፡፡ አንድና አንድ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሚመራ መንግስት በአገሪቱ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከሶስት እስከ አምስት ወር ውስጥ በጠብመንጃ ኃይል ስልጣን እንይዛለን ብለው የሚያምኑ ኃይሎች ሙከራም ቅዠት እንጂ እውን ሊሆን አይችልም፡፡

**የመገናኛ ብዙሃን ሚና:** መገናኛ ብዙሃን በሰላም ትምህርት በተለየም በክልሎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማጥበብና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩ ዜጎችን ልምዶችና እውነታዎችና በማስተዋወቅ ረገድትልው ሚና ይጫወታሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመምህራኖቹ ጋር የነበረውን ውይይት ሲያጠናቅቁም ኢትዮጵያ የሚያቆሟት አያሌ ምሰሶ ያላት አገር ናት በማለት ሁሉም ይህንኑ ለማጠናከር እንዲሰራ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

//